## ግልጽ ደብዳቤ

## ለክቡር  የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፖብሊክ መንግስት ጠቅላይ ሚንስተር

## ዶክተር አብይ አህመድ

### ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም !




ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ይዘውት የተነሱት በፍቅር፣ ሰላም፣እድገት፣ ይቅር መባባል፣ አንድነትና የመደመር መዝሙር የታጀበ የቀን ጅቦችን እየታገለ ዴሞክራሲና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ኢትዮጵያችን በአንድነት፣በእድገትና በብልጽግና ኣሸብርቃ በከፍታው ማማ ላይ ደምቃ እንድትታይ እያደረጉት ያለውን የቁርጥ ቀን ኢትዮጵያዊ ተግባር ስለሆነ ምንም እንከን ሳያጋጥመው ከታሰበለት ግብ እንዲደርስ ከልብ ስለምፈልግ እንደ ካሁን በፊቱ መሪዎች ላይ የተደረገው እያጨበጨብኩ ገደል እንዲገቡ ማድረጉ የአንድ ዜጋ ተግባር መስሎ ስለማይሰማኝ እንደ ወንድም እየወቀስኩና መስተካከል ይገባዋል የምለውን በእድሜ ውስጥ ያካበትኩትን ልምድና ኣስተያየቴን እየለገስኩ መደመር መምረጤን ስገልጽልዎት በደስታ ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚንስተር ! ከዚህ አኳያ ነው ቀጥሎ ያሰፈርኩትን ሃሳብ እንዲገነዘቡልኝ የምማጸንዎት።

በ1967 ዓ/ም የኢትዮጵያ አብዮት ሲፈነዳ እርስዎ ምናልባት የሁለት ዓመት ህጻን የነበሩ ይመስለኛል።”ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም “ የሚለውን የዚያን ግዜ መፈክር የመጀመርያ ትውስታየ ማድረጌ ያለምክንያት እንዳይመስልዎት። በንጉሱ ከፍተኛ ምሬት የነበረው በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በፈጣሪ የተሰየሙ፣ ከወደቁ ኢትዮጵያ ትቀሰፋለች ሲባልላቸው የነበሩ ንጉሰ ነገስት ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለስላሴ በህዝብ እንቅስቃሴና በደርግ አስተባባሪነት ከስልጣናቸው ወርደው ከዙፋናቸው ስር ተቀበሩ። ንጉሱ ሲያደርሱት የነበረውን ግፍና ሰቆቃ ያንገሸገሸው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ የተማረው ክፍል በንጉሱ ስርዓት እንዲያ መገርሰስ ፈነደቀ። የህዝብ እንቅስቃሴን የሚመራ የተጠናከረ ፖለቲካዊ ፓርቲ ባለመኖሩ ስልጣኑን የተቆጣጠረው

ግዝያዊ አስተዳደር ደርግ ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም የሚል መርህ አንግቦ በከፍተኛ የአገር ፍቅር ስሜት የእድገት በህብረት ራእይን እየዘመረ ነበር እንቅስቃሴውን የመራው።

ያለምንም ደም ኢትዮጵያን የማስቀደም ራእይ የሚነቀፍ አይመስለኝም። በመሳፍንትና የንጉሳን ቤተሰብ ተይዞ የነበረውን ለም መሬት ለገበሬው አከፋፈለ። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመሰለው አመለካከት በፓርቲ እንዲደራጅ ስለተፈቀደለት ወዝሊግ፣ ኢጭአት፣ኢማሌድህ፣ መኢሶን፣ ሰደድ አረ ስንቱ ፓርቲዎች እንደ አሸን ፈሉ።በቅንነትና ያለምንም ደም ኢትዮጵያን ለማስቀደም የተነሳው ሃይል በዙርያው የነበሩት የተለያየ አጀንዳ የነበራቸው ስግብግብ ጅቦችን መለየትና ፈር ማስያዝ ስላቃተው ግን የኢትዮጵያ ትቅደም ባቡር ሃዲዱን ሳተና በነዚያ አሰፍስፈው ከበውት በነበሩ ስግብግቦች መዳፍ ስር ወደቀ። ጸረ ህዝብ ተግባሮች ተበራከቱ። በፖለቲካ ፓርቲ የተሰባሰቡት ታረዱ። በቀላሉ በውይይት መፈታት ይችሉ የነበሩ የህዝባዊ መንግስትና ሌሎች የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ያነገቡ ኢትዮጵያውያን

የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት፣

እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት፣

የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች፣

ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች።

እየተባለ ከፉኛ ተመቱ። ግፍ በዝቶብናል ከኢትዮጵያ ጋር መኖር አንፈልግም ያሉትን የኤርትራ ወንድሞቻችን ጥያቄያቸው በሰላምና በዴሞክራስያዊ መንገድ ለምፍታት እንደ መሞከር የማሳዋንና የአሰብን ወደብ ብቻ ታሳቢ በማድረግ ጸረ አብዮት፣ ተገንጣይ እየተባለ በህዝብ ላይ መገመት ከሚቻል በላይ ግፍ እንዲደርስ አደረጉ። በኤርትራ ብቻ አላበቃም። በኦሮምያ፣ በትግራይ፣በአማራ በደቡብ ስንቱን ቆጥሮ ይዘለቃል ከፍተኛ ግፍና በደል ተፈጸመ። ያለምንም ደም ብሎ የጀመረው አብዮት ኢትዮጵያን በደም አጥለቀለቃት። በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን ወጣቶች በየጎዳናው ተዘረሩ። ፍትህ ጠፋ። ዴሞክራሲ ለሽታም አልገኝ አለ። እንኳንና የተቃወመ፣ የተሰለፈና የተደራጀ ያሰበም ወንጀለኛ ጸረ አብዮት እየተባለ ተቀጠፈ። ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ብለው ቅን አላማ አንግበው የተነሱ ኢትዮጵያውያን በዙርያቸው በተሰገሰጉ አውሬዎች ምክንያት መንገዳቸውን ስለሳቱ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን አንግበው የተነሱት ዜጎችን ጨፈጨፏቸው። ይህ ተግባራቸው የህዝብ ቁጣና ዓመጽን ቀሰቀሰ። እንደ ህወሓት፣ ኢህአፓ፣ ኦነግ፣ሲአን ኢድህና ሌሎች ንቅናቄዎች እንዲነሱና እንዲጠናከሩም በር ከፈተ።

ህዝባዊ ዓመጹ በተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች እየተመራ እንደወላፈን ተቀጣጠለ። ወላፈኑ የተሰገሰጉትን ሌቦቹ፣ ጅቦቹንና ግፈኞቹን ብቻ ሳይሆን እነሱን ያቀፉ ያለምንም ደም በለው የተነሱትንም ሳይቀር ፈጃቸው። እስር ቤት አጎራቸው። በስደትም በታተናቸው። ያለምንም ደም ብለው የተነሱት የከበብዋቸውን አውሬዎችና ጅቦችን ማጽዳት ባለመቻላቸው ምክንያት መጨረሻቸው ቤተክርስትያን እንደገባ ውሻ ሁሉም ህዝብ የሚያሳድዳቸው ሰይጣን እንዲሆን አበቃቸው። ለዘለአለሙ ወደማይመለሱበት መቃብርም አጋዛቸው። የአገሪቷ እድገትም ባለህበት ሂድ ሆኖ ቀረ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሉታል ይህ ነው።

ክቡር ዶክተር አብይ አህመድ !

አንዳንድ ሰዎች እርስዎ ወደ ስልጣን የመጡበትን መንገድ ሲረግሙና ሲተቹ ይገርመኛል። አንዳንዶቹ መፈንቅለ መንግስት ነው ሲሉት ሌሎቹ ደግሞ የተደራጀ የቡድን ስራ ነው ያመጣቸው ይላሉ። የተባለ ይባል። እኔ እስከተከታተልኩት ድረስ የአንጋሾች አፈናን ዘልቀው፣ በአብዝሃው ድምጽ ተደግፈው የኢህአዴግ አሰራር በሚፈቅደው መሰረት ህገ ደንቡን ተከትለው ለኢህአዴግ ሊቀመንበርነትና ከዚያም በቆየው አሰራር ለጠቅላይ ሚንስትርነት ደርሷል። ሳይሆንለት ቀርቶ ነው እንጂ ሁሉም ተደራጅቶ እንደገባ ባህር ማዶ ላለነውም ሳይቀር ዜናው ደርሶናል። በዚህ ግራ የሚጋባ ካለ ተባለንዴ ብሎ ከማለፍ ውጭ ምንም ማለት አይቻልም። የጠቅላይ ሚንስተርነትን ቦታ ከተረከቡ በኋላ ደግሞ ሕገ መንግስት በሰጥዎት ሃላፊነት መንቀሳቀስዎ ተገቢ ነው። የፓርቲና የመንግስት ተግባር እየተቀላቀለ ሕገ መንግስታዊ ስልጣን የሌላቸው ሰዎች ከኋላ ተቀምጠው የመንግስትን ባቡር መሪ ይዘው እንዳያሽከረክሩ መከልከልዎ ከተገቢም በላይ አስፈላጊ ነው።

አከታትለውም በርካታ ልባችንን የሚያርሱ አጀንዳዎችን ይዘው ተነስቷል። ቂም በቀል ይቅርና በፍቅር እናሸንፍ ! ሰላም ይስፈን እድገት እናስመዝግብ ! ዴሞክራሲና ፍትህ ይንገሱ ! ለሕገ መንስታችን ታዛዦች እንሁን ! ሙስና ቀይ መስመራችን ነው ! የቀን ጅቦችን በማንቁርታቸው ይዘን የዘረፉትን እናስመልስ ! ስንኖር ኢትዮጵያውያን ስንሞት ኢትዮጵያ ነን ! አንድ እንሁን እንደመር ! የሚሉ መፈክሮችዎ በሚገባ ወድጃቸዋለሁ።

”ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነውና“ ይህ ሰው ምነው ወሬ አበዛ ሲሉ ጆሮየ ውስጥ አይገባም። ተግባርዎም እንደ ንግግርዎ መሆኑን ተገንዝቤአለሁና። በተለያዩ ምክንያቶች ነጻነታቸውን አጥተው በእስር ሲሰቃዩና ሲማቅቁ የነበሩ ወገኖቻችንን አስፈትተዋል። ይህ ላልታሰረ ሰው ቀላል ይመስላል። መብቱ ተገፎ ከቤተሰቡ፣ ከልጆቹ፣ ከወላጆቹና አብሮ  አደጎቹ ተለይቶ ጨለማ ውስጥ ሲኖር ለነበረ ሰው ምን ማለት እንደሚሆን ግን መገመት አይከብድም። በተለይ ባልዋሉበት ጉዳይ ፍትህ በማጣትና የኛ ነው በሚሉት መንግስት ለታሰሩና ለተጠቁ ምንኛ እንደሚከነክን መረዳት አያስቸግርም። በዚህም አላበቃም። በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የከራከርላቸው የመንግስት አካል አጥተው ወህኒ ተወርውረው የነበሩ ዜጎቻችንን አስፈትተው በዲፕሎማስያዊ ፕሮቶኮል ሳይኮፈሱ እርስዎን ለማጓጓዝ በተመደበ አውሮፕላን ጭነው አገርዎ  ሲገቡ እያየ ልቡ ቅቤ የማይጠጣ ኢትዮጵያዊ ካለ የተረገመ ብቻ ነው። ችግር ተፈጠረ በተባለበት አከባቢ እከሌ ካድረ ወይ ሚንስተር ሂድና አስተካክለህ ተመለስ ማለት እየቻሉ ራስዎ ተጉዘው ከህዝብ ጋር ቁጭ ብለው ችግሮችን በውያይት አርግበው ሲመለሱ ማየት ምን ያህል የህዝብ ፍቅር እንዳልዎት አሳይቶኛል። ከጎረቤት አገሮች ጋር ፍቅርና መከባበር እንዲነግስ ያደረጓቸውን ጉዞዎችና ያስመዘገቡት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ድሎችም ኮርተናል። በጸረ ዴሞክራሲያዊ ተግባራቸው በህዝብ የተጠሉና ለመድረኩ ብቁ ያልሆኑትን አንጋሽ አመራሮችንና ጋሻጃግሬዎችን በድፍረት ማሰናበትዎ እኔንና መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ የልብ ልብ እንዲሰማን አድርጎናል። በግራም በቀኝም የነበሩ ተቃዋሚዎችንና አማጽያንን ወደ አገራቸው ገብተው በሰላም የመሰላቸውን ሃሳብ ይዘው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግዎ ሌላው በአገሪቱ ውስጥ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲስፋፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ተግባርዎ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ አንዳንድ ሆዳምና በሽዎች መስዋእት የከፈለው ህዝብን የካዱ የእድሜ ልክ መሪዎች ሆነው መኖር የሚያምራቸው ግለሰቦች በፈጠሩት መሰሪ ተግባርና ጸረ ህዝብ የስልጣን ተስፈኞች ያለመታከት በሚያራግቡት አሉቧልታ ምክንያት በትግራይ ህዝብ ላይ የተዛባ አመለካከት እንዳይያዝ የሚያቀርቡት ሃሳብና ምክር በህዝቦች ላይና በአገር አንድነት ትርጉም ያልዎትን ንጹህ አመለካከት ቁልጭ አድርጎ አሳይቶኛል። እነዚህ ሁሉ የተከናወኑት በሶስት ወራት ውስጥ ብቻ መሆናቸው ደግሞ  ድሉን እጥፍ ድርብ አድርጌ እመለከተዋለሁ። እነዚህ ሁሉ ሃሳቦችዎና ተግባሮችዎ ናቸው ከጎንዎ ተሰልፌ ያለማመንታት እንድደግፍዎትና እንድደመር የገፉፉኝ።እኔም ተደምሬአለሁ።ተደምሬአለሁ ካልኩ ደግሞ በቃ ! ተደምሬአለሁ ማለት ነው።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስተር  !

የተነሱለትን ዓላማ እንድደግፍና እንድደመር የወሰንኩበት ሌላ ምክንያትም አለኝ። እምብዛም የማንኮራበት የኢህአዴግ/ ህወሓት አመራር የዴሞክራሲ ግንዛቤና ተግባር ከግዜ ወደ ግዜ እየከፋ በተለይ ደግሞ መንግስት ከተመሰረተ በኃላ ሁሉም ነገር በህግና ስርዓት ይጓዛል ብለን ተስፋ የጣልንበት አልሻሻል እያለ ስላስቸገረን ባገኘነው መድረክ ታግለን በጥቅም፣ አምቻ ጋብቻና፣ በቡድን የተቆራኘውን ሃይል ማሸነፍ ባለመቻላችን በአመለካከታችን ምክንያት እኛም እንደ ሌሎቹ ንጹሃን በአይነ ቁራኛ ከመታየት አልፎ ሰብአዊ መብቶቻችንን መግፈፍ ስለጀመሩ በስደት እንድንኖር ምክንያት ሆኖናል። በፓለቲካ ፓርቲ አባልነት መታቀፍ አልወድም። ወደ አገሬ ተመልሼ እንዳልገባም የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ አልገፋፋኝም። የአገሬ ጉዳይን ሳስብ የፈለግሁትን ያህል እንቅልፍ ባላገኝም በስደት በሰላም እኖራለሁ። እግዚአብሄር በአገራችን ያጣነውን ሰላምና ዴሞክራሲን ተጎናጽፈን እንድንኖር ያደረገችን ሁለተኛ አገራችን ዩ ኤስ አሜሪካንና ህዝቧን ይባርክ። በዩ ኤስ አሜሪካ የምንኖርና ስለአገራችን ጉዳይ የምንጨነቅ ኢትዮጵያዊያን ነኝ።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትራችን !  እነዚህ ይዘዋቸው የተነሱ አልማዞች ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ ጀምሮ ኢትዮጵያን በደም ጎርፍ እንድትጥለቀለቅ ያደረገ አደጋ እንዲያጋጥማቸው ስለማልመኝ የሚመስለኝን ምክር ለመለገስ ብእሬን አንስቻለሁ። ጠቃሚ መስሎ የሚታይዎትን ያንሱ። ይህን ሃሳብ የሚጋራ ኢትዮጵያዊ ካለም ደስታየ ወሰን አይኖረውም እንገናኝ እንነጋገር ባይ ነኝ።

በመጀመርያ ማንሳት የምፈልገው ጉዳይ ስለ ሕገ መንግስታችንና ሕገ መንግስታዊ ስርዓታችን ነው። ሕገ መንግስት በአጭሩ ምን ዓይነት መንግስት መመስረት እንዳለበት፣ የመንግስት መዋቅር ምን መሆን እንደሚገባውና እያንዳንዱ መዋቅር የሚኖረው ስልጣንና መዋቅሮቹ እርስ በርሳቸውና ከህዝብ ጋር የሚኖራቸው ዝምድና ምን መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ፣ የዜጎችን መብት የሚዘረዝር፣ መንግስት የሚከታላቸው አቅጣጫዎችን የሚያብራራና የመንግስትን ስልጣን የሚገድብ ህጋዊና ፖለቲካዊ ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ ዜጎች ተስማምተው የሚያጸድቁት በህዝቦች መሃከል የሚደረግ ማህበራዊ ውል [Social contract] ነው። ይህ ሰነድ በአገሪቱ ውስጥ ካሉ ህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ነው። በአገራችን ውስጥ የተረጋጋና አስተማማኝ ስርአት ሊኖር የሚችለው ሁሉም ህዝብ እርስዎንም ጨምሮ በሕገ መንግስት ብቻ መመራት ሲችል ነው። የእርስዎ ፓርቲ ሹማምንትና ባለስልጣናት ሕገ መንግስቱን አላከብር እያሉ ከህግ በላይ ሆኖውብናል ብለን ደም አንብተናል። ከመፈክሮችዎ አንዱ የህግ የበላይነት እንዲከበር መታገል ነው። አሁን ህግ እየተጣሰ ነው ብለው የሚነሱ ዜጎች ሲያጋጥምዎት ትላንትና ብዙ ጥሰት አልነበረም ወይ ! የሚል መልስ እንዲያሰሙን አልጠብቅም። የትላንትናው የተጠላው ጥሰት ለአሁኑ ጥሰት ዋስትና አይደለምና። ዜጎችን ከእስር መፍታት ያስደስታል። እነሱን ያሰረ ህግ ሳታስወግድ መፍታት ግን ከህግ በላይ መሆንን ያስከትላል። ይህ ደግሞ እርስዎም አይፈልጉትም። እኔ ከፍተኛ ትኩረት እንዲያደርጉለት የፈለግሁት ግን ሌላ ጉዳይ አለኝ። የለውጡ ደጋፊዎች ነን እያሉ ከዙርያዎ ከተሰበሰቡ ውስጥ ሕገ መንግስቱን የማይቀበሉ እንዳሉ በግልጽ እየታየ ነው። በተለይ ፌደራሊዝሙን አይቀበሉትም። ምርጫቸው የድሮ ዓይነት ወጥ ኢትዮጵያን ነው። በቋንቋና በባህል የተደራጀው አወቃቀር ደግሞ እንደ ነቀርሳ ይመለከቱታል።መሬት በመንግስት ስር ይሁን የሚለው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ እንደ እሬት ይመራቸዋል። በተለይ የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው አንቀጽ አገርን ይበትናል እያሉ አጥብቀው ይኮኑኑታል። በዚሁ በአሜሪካን አገር የነበሩ ሕገ መንግስቱን ሲያቃጥሉት በአይን ብሌኔ ተመልክቻለሁ። ኢትዮጵያ ውስጥም እየተደገመ ነው። አለመቀበላቸው መብታቸው ነው። ሕገ መንግስት ማለት መጽሃፍ ቅዱስ ወይንም ቁርአን ማለት አይደለም። ህዝብ ባልፈለገው ሰአት ሊተረጉመው፣ ሊያሻሽለውና ሙሉ በሙሉ ሊቀይረው ይችላል። ነገርግን ህግንና ስርአትን በተከተለ መንገድ መሆን ይኖርበታል።እነዚህ ሰዎች እነሱ የሚፈልጉትን የማይቀበል ሰው እንዳለም ማወቅና መገንዘብ ይኖርባቸዋል። በፌስ ቡክ እየተቀባበሉ በማስወራት ወይንም በጫጫታና ሁከት የህዝብን መብት በመጣስ የራሳቸውን አመለካከት መጫን በሚፈልጉ ሰዎች እየተከበቡ እንዳሉ ይታየኛል። የኢትዮጵያ ህዝብ መሬት በግል ይተዳደር መሬት መሸጥ መለወጥ አለበት ብሎ ከተቀበለው መብቱ ነው።አርሶ አደሩ በድርቅ ወይንም በሌላ ችግር ሲጠቃ መሬቱን ለሃብታሞች ሸጦ ለዘለአለሙ እትብቱ ከተቀበረበት መሬት ስሩ ተነቅሎ መጥፋትን እፈልጋለሁ የሚል ከሆነ ምርጫው የሱ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በፌደራሊዝም አንተዳደርም እንደ አጼ ሃይለስላሴና ደርግ ዘመን አንድ ወጥ መንግስት እንፈልጋለን ካለም አሁንም ምርጫው የህዝቡ ነው። ፌደራሊዝም እንቀበላለን በቋንቋና በባህል መካለሉን ግን አንፈልግም እንደ ድሮ በወንዝና በተራራ ተከፋፍሎ የኦሮምያ ክልል ሃረር፣ ባሌ፣ ወለጋ፣ አሩሲ ወዘተ ተብሎ የአማራም ወሎ ፣ ጎጃም፣ ጎንደር ወዘተ ተብሎ ሌሎችም እንዲሁ በድሮው መልክ ተከፋፍሎ መካለሉ ይሻለናል የሚሉ ከሆነም መብታቸው ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ መሆን የሚችለው ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን ተከትሎ በህግና በስርአት በህዝብ ነጻ ውሳኔ ብቻ መሆን ይኖርበታል ባይ ነኝ። የህዝብ እውነተኛና ነጻ ሃሳብን በማያምኑ ነውጠኞች ከተከበቡ ግን ከሃዲዱ ለመውጣት ብዙ ግዜ አይወስድብዎትም። እነዚህ ሰዎች አላማቸውን ለማሳካት ማለፍ ካልቻሉ ደግሞ የመጀመርያ ጠላቶችዎ እንደሚሆኑ እንዲያስተውሉ እፈልጋለሁ። የያዙት አላማ አገርን ያድናል። ከዙርያዎ ያሉትን በህግና በስርአት እንዲሄዱ ካላደረጉ ግን ይቅርታውም፣ሰላሙም አንድነቱም እድገቱም መደመሩም መንገዱን ይስትና ትርምስ ይፈጠራል። መደመር ቀርቶ አገርን ይበታትናል፡፡ ብሎም አገርን በደም ያጥለቀልቃል። ክቡር ጠቅላይ ሚንስተር ይህን አንድ ይበሉልኝ ።

ሌላው በየሰልፉ የሚታዩ ባንዴራዎች፣ መፈክሮችና ምስሎች ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ባጸደቁት ሕገ መንግስት አንቀጽ 3 ባንዴራችን አረንጓዴ ብጫና ቀይ ቀለማት ሆኖ በማሃሉ ብሄር ብሄረሰቦችን ይወክላል የተባለ አርማን አስፍሯል። በተጨማሪ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 48/1999 በዝርዝር ባንዴራው እስከነምስሉ አስፍሯል። ይሁን እንጂ በቅርቡ በተደረጉ ሰልፎች ይህ ባንዴራ አልታየም ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ሰልፈኞች ብመሃል ያለውን አርማ ቀደው በማውጣት ሲያውለበልቡት ታይቷል። ባህር ዳር በተደረገው ሰልፍ ከ500 ሜትር በላይ የድሮ ባንዴራ ተሰርቶ ሲውለበለብና በሕገ መንግስት የጸደቀው ባንዴራ ቀርቶ በምትኩ የኤርትራ ባንዴራ ሲውለበለብ ታይቷል። በህገ መንግስት የጸደቀው ባንዴራ ለምልክትም አልነበረም። የኮለኔል መንግስቱ ምስልም በአደባባይ ከፍ ብሎ ታይቷል። በጣም የሚያሳዝነው ጉዳይ ደግሞ ኢትዮጵያን በምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት ይመራሉ ተብለው የተሰየሙ ባለስልጣን ዋነኛው እንግዳ ሆነው መቅረባቸው ነው። ባንዴራውና ሕገ መንግስቱን የማይከላከል መሪ እንዴት በስለጣን ይቀመጣል？ይህ ሁሉ ምንን ያመላክትዎታል？እንዲህ የሚያደርጉትስ እነማን ናቸው

? እነዚህም እንደመር እያሉ ከዙርያዎ እየተኮለኮሉ ናቸው። በእኔ በኩል ማንም ሰው እንኳንና የኮለኔል መንግስቱ ምስል የይሁዳ ምስልም ይዞ ቢሰለፍ ቅር አይለኝም። ተሰላፊዎቹ የማንን አላማ ሊያነግሱ እንደተነሱ ግን ኮለል አድርጎ ያሳየኛል። የራስህን ባንዴራ ወደ ጎን በመተው የሌላ አገርን ባንዴራ ተሸክመህ መውጣትስ ምንን ያመላክታል? በዚህ ባንዴራ የትግራይ፣ የኦሮምያ፣የሶማልያ፣ የዓፋር፣የሲዳማ፣የወላይታና ሌሎችም ህዝቦች ምን ይሰማቸዋል ብለው ይገምታሉ? በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የጸደቀው ባንዴራ በባህርዳርና ሌሎች ከተሞች ሲዋረድ በአስመራ ግን ተከብሮ ሲውል ምን ይሰማዎታል? የጠቅላይ ሚንስትርነትን ስልጣን ሲረከቡ የተረከቡት የአገሪቱ ህጋዊ ባንዴራና ሕገ መንግስቱን እንዴት ነው የሚከላከሉለት? በአገሪቱ ህግ ተመዝግበው በህግ ያልጸደቁ ባንዴራዎችስ የማን ተብለው ይውለበለባሉ? እሺ ሃሳብ የመግለጽ መብት አርማና ባንዴራ ይዞ የመውጣት መብትንም ሊያካትት ይችላል የሚል ክርክር ሊያስነሳ ይችላል እንበል። የመንግስት ከፍተኛ ሃላፊ እዚህ ውስጥ ከተዘፈቀ ግን ጉዳዩ ሌላ መልክ መያዝ ይኖርበታል። ክቡር ጠቅላይ ሚንስተር የሁሉም መደመር ጥሩ ነው። ነገር ግን ህግንና ስርዓትን በተከተለ መንገድ ማድረጉ ምንም አማራጭ የለውም። ዋናው ልገልጽልዎት የምፈልገው ነጥብ አንዳንዴ ፖለቲካ ቆሻሻ ጌም ነው። የፍቅር፣ይቅርታና መደመር ቅን ሃሳብዎ ሃዲዱን እንዳያስቱትና አገሪቱን ለመበታተንና በደም እንድትጥለቀለቅ ለማድረግ እንዳይጠቀሙብት ሁሉም ሰውነትዎ አይንና ጆሮ መሆን ይኖርበታል እላለሁ። እውነተኛ ፓርላማ ካለና እርስዎም የአገሪቱን ሕገ መንግስትንና ባንዴራ የመከላከል ከፍተኛና ሕገ መንግስታዊ ሃላፊነት ስላልዎት ምክትል ጠቅላይ ሚንስትሩ በሕገ መንግስት የጸደቀ ለምልክት አንድም ባንዴራ በሌለበት ነገር ግን በሕገ መንግስት ያልጸደቀ ከተለመደው ውጭ በ500 ሜትር የተሰራ ባንዴራ መድረኩን በተቆጣጠረበት መድረክ እውቅና ሰጥተው ለመግለጫ መቅረባቸው ሕገ መንግስታዊ ተአማኒነታቸው ጥያቄ ላይ የሚጥል ስለሆነ በያዙት ሃላፊነት የመቀጠል አስፈላጊነት ከፓርላማውና ከኢህአዴግ ጋር ቢነጋገሩበት የሚል ሃሳብ አለኝ። የክልሉ ፕረዚደንት ስልጣን ጉዳይ የክልሉ ህዝብ ስልጣን ስለሆነ ከእርስዎ የስልጣን ክልል ውጭ ይመስለኛል። የኢህአዴግ አባልነታቸው አስመልክተው ግን ጉዳዩን ማንሳት የሚችሉ ይመስለኛል። ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ይህን ሁለት ብለው ይያዙልኝ።

የቀን ጅቦችን አስመልክቶ አንድ እምነት አለኝ። የጅብ መነኩሴ ስለሌለ “የአገሬ ጅብ ይብላኝ” የሚል አባባል አይጥመኝም። ከየትም ይምጡ ጅቦች ያው ጅቦች ናቸው። እርስዎ የሚያዘወትሩት የቀን ጅቦች ላይ ብቻ ነው። አባባልዎን በትክክል ይገቼው ከሆነ በዓይን ብሌናችን እያየናቸው በጠራራ ጸሃይ የሚቦጭቁ ማለትዎ ይመስለኛል። አዎን እነዚህ ህዝብ አምኖ ሃላፊነት የሰጣቸው ስልጣንን መከታ በማድረግ ሌላው ህዝብን ሞኝ አድርገው ከድሃ አፍ የሚመነትፉ ሌቦች ግፈኞች ናቸውና በነዚህ ላይ ምህረት አያስፈልግም።ነገር ግን የጨለማ ጅቦችና የበግ ለምድ የለበሱ ቀበሮዎችም አብረው መኸርልጧልና ትኩረት እንዳያጡ አደራ። እንደ ትናንትና ሙሰኞችን ይዘናል እያሉ የቀበሌ ድሃዎችን እየሰበሰቡ ወደ ቴሌቭዥን እያመጡ እንደማያሳዩንም እርግጠኛ የምሆን ይመስለኛል። እኛ የምንፈልገው አውራዎቹን ነው። የምንፈልገው ደግሞ መታሰራቸው ብቻ አይደለም። የሃገር ሃብቱ ገንዘቡንና ንብረቱንም ጭምር ነው። እንዴት ተደርጎ ነው እንዚህን መለየት የሚቻለው ብለው አይስጉ። መልሱ ያለው ከህዝቡ ጋር ነው። አሁን የሚልዮኖችን ድጋፍ አግኝተዋል። ከእነዚህ ሚልዮኖች የሚሰወር ምንም ነገር ሊኖር አይችልም። የሚያስፈልገው መረጃው የማሰባሰብ ስርአቱን ማበጀት ነው። የመንግስት ሰራተኛ ገቢ ይታወቃል። የነጋዴ ካፒታልና ትርፍ መደበቅ አይቻልም። በልጆች፣ በሚስት በባል፣ በወንድምና በእህት፣ በአባትና እናት ወዘተ የሚደበቅ ምንም ነገር መኖር የለበትም። ይህ ሌብነት ላንዴና ለመጨረሻ ከስሩ መነቀል አለበት። የሌብነት ተግባር ነውር ተግባሪውም ነውረኛ ሌባ እንደሆኑ በተግባር ማስተማር ይጠበቅቦታል። ውጭ አገር ያለችው እህቴ፣ ወንድሜ አጎቴ ላከልኝ በሚል ማምለጥም አይፈቀድም። እኛ ከውጭ ተሰልፈን እናግዝዎታለን። ጅቦቹ ከሰሜን ከደቡብ ከምስራቅና ምእራብ እንደሆኑ ደግሞ እንዳይዘነጉ። በተለይ በኢህአዴግ አመራር የነበሩ፣ በሚንስትርነት፣ በመምርያና በቢሮ ሃላፊነት ደረጃ ያሉና የነበሩ አጥርተው ለህዝብ ያቅርቡልን። ከዙርያዎ ከሚሰለፉ እርስዎን ተገን በማድረግ አዳዲስ ጅቦች እንዳይፈጠሩ ደግሞ አደራ በሰማይ አደራ በምድር። ይህን ሶስት ብለው ይያዙልኝ።

በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራርና ደጋፊዎች እንዲሁም ጉዳዩን በውል ያልተገነዘቡ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ እያካሄዱ እንደሆኑ ተገንዝቤያለሁ። በግልጽ እንነጋገር ከተባለ አንዳንዶቹ ከህወሓት አልፈው ወያኔ ትግሬ እያሉ በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የማጥላላትና የመደመርን ርእዮት የሚጻረር እንቅስቃሴ የሚያካሂዱ እንዳሉ እርስዎም የሚስቱት አይመስለኝም። በትግራይ ህዝብ ላይ ማነጣጠራቸውን በጉልህ የሚያስረዳ ሌላ ነገር ልጨምርልዎት። ህወሓትን አሸንፎ ስልጣን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ትንቅንቅ በማካሄድ ላይ ባለውና አባላቱ የሚታሰሩና

የሚገደሉ እንደሆኑ ባሻቸው ግዜ ለዜና የሚጠቀሙበት ዓረና ትግራይ ፓርቲን ሳይቀር የተመሰረተው በትግራይ ተወላጆች ስለሆነ ብቻ የማጥላላት ዘመቻ ሲከፍቱበት ይስተዋላል። ዓረናና ህወሓት ስህተት የላቸውም ለማለት አይደለም። በዚያ ልክ ከሌላ ብሄር በተፈጠሩ ፓርቲዎች ላይ ምንም የሚያነሱት ሂስ አለመሰማቱ ግን ምንን ያመላክታል？ የትግራይ ህዝብ ምን ዓይነት ኢትዮጵያዊ እንደሆነ በውል ያውቁታል። ታድያ ይህ ተግባር የዶክተር አብይ የመደመርና የፍቅር አላማን የሚከተል አመለካከት ነውን？የሚወስደንስ ወዴት ነው？ለምንስ ነው የትግራይ ህዝብ እንዲነሳ የሚጎነትሉት？ክቡር ጠቅላይ ሚንስተር የመደመር መፈክርዎ በቀናሾች እየተከበበ ነውና አንድ ቀን ቁጭ ብለው ለምንድነው እንዲህ እያደረጉ ያሉት？ እነማንስ ናቸው？ ብለው እንዲያጤኑትና ገና ከእንጭጩ የማያዳግም እርምጃ እንዲወስዱበት ብክብር እጠይቅዎታለሁ።

እርስዎ በግልጽ ቋንቋ የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንድ አይደሉም። የትግራይ ህዝብ ልዩ ተጠቃሚ አድርጋችሁ የምትመለከቱ ሰዎች ሂዱና ትግራይን ጎብኙ እስከ አሁን ድረስ በውሃ ጥም የሚቸገር ህዝብ ነው ያሉትን ተከታትያለሁ። ከዚህ አባባልዎ ጋር በሚገባ እስማማለሁ። የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንድ አይደሉም። ህወሓት አንድ አይነት አላማ ላይ የተስማሙ ግለሰቦች የመሰረቱት ተቋም ነው። የፓርቲውን ዓላማ የሚነድፉና አመራሩን የሚመርጡ ያው የድርጅቱ አባላት ብቻ ናቸው። የትግራይ ህዝብ የህወሓትን አመራር መርጦ አያውቅም። የማይፈለጉ በላዩ ላይ ጸረ ዴሞክራስያዊ ተግባራትን የሚፈጽሙና ሙሰኞች አመራር ሳይቀር የማውረድ መብት የለውም። በፍጹም አይችልም። ህወሓት የፓለቲካ ፓርቲ ስለሆነ ለዚህ የተመቻቸ አሰራርና መመርያም የለውም። ስለዚህ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ የተለያዩ ናቸው።

ሌላ ነጥብም ልጨምርልዎትና እነዚያ ጸረዴሞክራሲና ሙሰኛ መሪዎችና ጋሻጃግሬዎቻቸውም የህወሓት ዓላማን ከድተዋልና የተለያዩ ናቸው። ንጽሁ ተጋዳላይና ኣባል ከነዚህ ሰዎች ሆድና ጀርባ ከሆነ ከርሟል። የትግራይ ህዝብ ከታገለለት ዓላማ ተስፋ ሲያጣ፣ የተማረው ትውልድ ስራ አጥቶ ሲንገላታና በአልባሌ ቦታ ሲውል ምን እናድርግ ብለው ጠይቀውት የማያውቁ፣ ፍትህ ሲጓደል፣ ዴሞክራስያዊ መብት በገፍ ሲጣስ፣ ለትግሉ አካላቸውን የከፈሉ የአካል ጉዳተኞች በበርካታ ችግሮች ሲሰቃዩ የታጋዩ ቤተሰብ ከፍተኛ እንግልት ሲያጋጥመው ዞር ብለው የማይጠይቁት አሁን ግዜ ሲከዳቸውና መሬት ሲጨልምባቸው የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንድ ናቸው እያሉ መሸሸግያ ዋሻ ለማድረግ እየሞከሩ ነው። ነገር ግን ሰሚ ጆሮ አያገኙም። በፍጹም አይቻልም።

ህወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ አይደሉም ብልም ግን እኔ እስከማውቀው ድረስ ህወሓት እንደ ድርጅት ይዞት የተነሳው አላማ ትክክለኛ ስለነበር በትግራይ ህዝብ ታቅፏል። የትግራይ ህዝብ በርካታ ልጆቹን ለህወሓት አስረክቧል። ከህወሓት ጋር ተሰልፎም ህይወት፣ ጉልበት ደምና ላቡን አንጠፍጥፎ ለድል አብቅቶታል። የአንዳንዶቹ መሪዎች እንደዛሬ ኣምባገነን ሳይሆኑ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ስለነበር የትግራይ ህዝብ እንደ ልጆቹ አቅፎአቸው መጥቷል። ስለዚህ የትግራይ ህዝብ እነዚያ ሌቦቹና ጸረ ዴሞክራስያውያኑ የሌሉበት የጠራው ህወሓት የኔ ፖለቲካዊ ድርጅት ነው ብሎ አቅፎና ደግፎ የሚይዘው ህይወቱ ሳይቀር የሚከፍልለት የትግራይ ህዝብ መሪ ፓርቲ እንደሆነ ወዳጅም ጠላትም ማወቅ ያለበት ሃቅ ነው። ይህንን ፓርቲ መንካት ማለት ከዶክተር አብይ የመደመር ራእይና ከትግራይ ህዝብ ጋር መቆራረጥ ማለት ብቻ መሆኑን ማስመር እፈልጋለሁ። በተጨማሪም ከአገር ተሰደው በፖለቲካና በትጥቅ የኢትዮጵያ መንግስትን ሲፋለሙ የነበሩ ፖርቲዎች አገር ውስጥ ገብተው በሰላም እንዲታገሉ በሚጠሩበት በአሁኑ ሰአት በህወሓት ላይና በትግራይ ህዝብ ላይ እንዲያ ማነጣጠሩ ምን ለማድረግ እንደታሰበ ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር እንዲገነዘቡት እፈልጋለሁ። አንዱን ፓርቲ ወደ አገር አስገብተን ሌላውን ፓርቲ ከአገር ለማባረርና የትግራይ ህዝብን ያለ መሪ ፓርቲ ለማስቀረት ነው እንዴ？ህወሓት በሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖችን ለአገር ክብርና እድገት በሺዎች አካላቸው ያጎደሉበት የትግራይ ህዝብ መሪ ፓርቲ ስለሆነ ይህንን ፓርቲ መንካት የመደመርን ቀይ መስመር ማለፍ እንደሆነ መገንዘብ ምንም አማራጭ የለውም።

እስከገባኝ ድረስ እውነተኛው ህወሓት ሊቀ መላእክት ስላልሆነ ምንም ስህተት አልፈጸመም ማለት አልችልም። ህወሓት አንዳንድ ስብእና የጎደላቸው ሰዎች እንደሚሉት አማራን ለማጥፋት የተነሳ ነው የሚሉትን አሳፋሪ አባባልን ወደ ጎን ልተወውና እንደ ማንኛውም ፓርቲ የፈጸማቸው እኔም ራሴ አንድ ሁለት ብየ ልቆጥራቸው የምችል ጉድለቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ እስማማለሁ። ይሁን እንጂ ከጅምሩ አላማውን ግልጽ አድርጎ፣ የትግል ስልትና ስትራተጂውን ቀይሶ የተነሳ በዓለም ከሚጠቀሱ ታላላቅ የትጥቅ ትግሎች ተርታ የሚሰለፍ በኢትዮጵያ ታሪክ አብይ ምዕራፍ የከፈተ ድርጅት እንደሆነ ቢመርም እውነታ ስለሆነ ሊዋጥ የሚገባው ሃቅ ነው ብየ አምናለሁ።

የህዝቦች መሰረታዊ መብቶችን የጣሰ፣ ዜጎች ከአገራቸው የመውጣት መብትን የከለከለ፣ አባላቱ ሃይማኖት እንዳይኖራቸው ያደረገ፣ አገርን በአፈሙዝ ብቻ የሚያስተዳድር በአፍሪካ ተወዳዳሪ ያልነበረው የጦር ሃይል የገነባው የደርግ ስርአትን በእልህ አስጨራሹ የትጥቅ ትግል ውስጥ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር አብሮ ነገርግን ዋናውን ሸክም ተሸክሞ ያንኮታኮተና የኢትዮጵያ ህዝብ እፎይታን እንዲጎናጸፍ ያደረገ ጀግና ድርጅት ህወሓት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ ሲደረግ ሁሉም ሊባል የሚችል የህወሓት ታጋይ እንኳንና ትርፍ ሊወስድ የሚገባውም አላገኘም። በጸረ ዴሞክራሲ ተግባር ተዘፍቋል የሚል ክሴታም እሱን አይነካም። በፍጹም።

ህወሓት ከወገኖቹ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን የብሄር ብሄረሰቦችን ቋንቋ፣ባህል፣ ራስን የማስተዳደር መብት እንዲከበር በጽናት የታገለና አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችን ያካተተ ፌደራላዊ ስርአትን እውን ያደረገ ሕገ መንግስት እንዲጸድቅ የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ድርጅት ነው። አዲሱ ትውልድ ትላንትና በነዚህ ህዝቦች ላይ ሲደርስ የነበረውን ግፍና በደል ለማወቅ ሊቸገር ይችል ይሆናል። ሃቀኛ የኢትዮጵያ ታሪክን የሚያነብና ወላጆቹን የሚጠይቅ ትውልድ ግን ሃቁን መገንዘብ አያዳግተውም። በተለይ እርስዎ ይስቱታል ብየ አልገምትም። ህወሓት አሁን በአገሪቱ ውስጥ የተመዘገቡ አኩሪ ድሎች እንዲመዘገቡም የራሱን ድርሻ አበርክቷል። ያን ያህል ለትግራይ ህዝብ ባለመስራቱ ነው የሚወቀሰው። እውነታው ይህ ሆኖ እያለ ጎንደር ውስጥ ለተከናወነ የመብት ጥሰት ተወቃሽ የሚያደርጉት ህወሓትን ነው። አዋሳ ላይ ለሚደረግ ጸረ ዴሞክራሲ ተግባር የሚኮነነው ህወሓት ነው። ወለጋ ውስጥ ለሚደረገው ዝርፍያ የሚኮነነው ህወሓት ነው። በጥሩ ምግባራቸው የሚመሰገኑም ይሁኑ በጸረ ዴሞክራሲና የህግ ጥሰት እንዲሁም በሌብነት መወቀስ የሚገባቸው በዚህ ተግባር ተጨባጭ ማስረጃ የተገኘባቸው፣ ኢትዮጵያን በማስተዳደር ላይ የነበሩ ሁሉም የኢህአዴግ አመራሮች ማለትም የህወሓት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድና ደኢህዴን አመራርና በተለይ ደግሞ በፌደራልና በክልል የነበሩ ከአቅማቸው በላይ በአዲስ አበባ፣ ባህር ዳር፣ ሲዳማ፣ ናዝሬት፣ መቀሌና አዋሳ ወዘተ ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎችንና ቪላዎችን የገነቡ፣ ቢልዮኖች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ባንኮች ያከማቹ፣ ልጆቻቸውን ከአቅማቸው በላይ ውጭ አገር እየላኩ የሚያስተምሩ ሹማምንት መሆን ሲገባቸው ለምን በአንድ ፓርቲ ህወሓት ላይ ብቻ ይነጣጠራል ? ለምንስ ከትግራይ ህዝብ ጋር ይተሳሰራል ?

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ሁሉም ህዝብ በመሰለው አመለካከት ተደራጅቶ በሚንቀሳቀስበትና በመደመር አገር እናሳድግ በሚባልበት በአሁኑ ዘመን በህዝቦች ላይ የተዛባ አመለካከት ባላቸው ሰዎች እየተከበቡ እንዳሉ ረጋ ብለው እንዲያስተውሉ እፈልጋለሁ። ይህን አራት ይበሉልኝ።

አሁን በአገራችን ውስጥ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጋብዘው በሰላም የያዙትን ዓላማ ለህዝብ እያቀረቡ እንዲያስተምሩና ህዝብ ሲቀበላቸው አገር የማስተዳደርን ሃላፊነት እንዲረከቡ በሩ ተከፍቶላቸዋል። ይህ የፖለቲካ ምህዳሩን የማስፋት ስራ አኩሪ ውሳኔ ነው። ነገር ግን በአገር ጉዳይ ሁሉም ፓርቲዎች ሃላፊነት እየተሰማቸው እንዲንቀሳቀሱ በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እፈልጋለሁ። በእርስዎ በኩል ደግሞ ከእያንዳንዱ የሚጠበቀው ምን እንደሆነ በውል አውቆ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ የህግ ማእቀፍ ማስቀመጥ የግድ ይልዎታል። ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ በር ማመቻቸት ነው የሚሆነው። እዚህ ላይ ማስመር የምፈልገው ጉዳይ አገሪቱን እየመራ ያለው የእርስዎ ፓርቲ ኢህአዴግን በሚመለከት ነው። በተደራጀ መንገድ የማይመራ ስራ ፈቅ ማለት እንደማይችል በውል መረዳት አስፈላጊ ነው። በተለይ አሁን ከአንድ ወጥ አሃዳዊነት እስከ ተለያይቶ የተለያዩ ግዛቶችን መመስረት የሚፈልጉ የተለያየ አመለካከት የያዙ ፓርቲዎች በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱበት ግዜ ስለሆነ ኢህአዴግን ከሙስና፣ ከጸረ ዴሞክራስያዊነትና ዝርክርክ አሰራር አጽድተው፣ የተዛቡና ከወቅታዊ ሁኔታዎችና የህዝብ ፍላጎት ጋር አብረው መራመድ የማይችሉ የፕሮግራሙ አንቀጾችን አስተካክለው ለውድድር እንዲዘጋጅ የማጠናከር ተግባርዎ ለሰከንድም ቸል መባል የማይገባዎ እንደሆነ ማስረገጥ እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ ውዥንብር ውስጥ መግባት የለበትም። በህጋዊ መንገድ በሚደረግ ምርጫ አሸናፊው ፓርቲ ስልጣን እስኪረከብ አሁን አገሪቷን እያስተዳደረ ያለው ፓርቲ ኢህአዴግ ከቦታው ላይ ያለ ስለመሆኑም በየግዜውና በግልጽ ያሳውቁን። ፈርሶ ከሆነም እንዲሁ። ይህን በማድረግ ስለአገራችን ሁኔታ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ የማግኘት መብታችንን እውን እንዲያደርጉልን እጠይቃለሁ። ይህን በአምስተኛ ተራ ቁጥር ያስፍሩልኝ።

እዚህ ላይ ልዩ ትኩረት የሚያሻው ሌላው አብይ ጉዳይ አለኝ። መቸም ብሄር ብሄረ ሰብ የሚል ቋንቋ ለመስማት የሚቀፋቸውና የኢህአዴግ መለያ ሃረግ እያስመሰሉ ኢትዮጵያ ብቻ በሉ ለሚሉ ሰዎች እንደማይጥማቸው ይገባኛል። የነሱን ጉዳይ ለግዜው ወደ ጎን ላቆየውና ኢትዮጵያ የሁሉም ብሄር ብሄረሰብ አገር ናት። ሁሉም ህዝቦች በአገራቸው ጉዳይ ላይ የኤኮኖሚ ተጠቃሚዎች ማድረግ ብቻ ሳይሆን በአገራቸው ወሳኙ የፖለቲካ ጉዳይና አገሪቱን በመምራት እኩል ተሳትፎ ሊኖራቸው

ይገባል። ኢህአዴግ አደረጋቸው ከምላቸው ትላልቅ ድክመቶች አንዱ አናሳ እየተባሉ የሚጠሩ እንደ ሶማልያ፣ዓፋር፣ ቤንሻንጉልና ጋምቤላ በኢህአዴግ ውስጥ ታቅፈው አገራቸውን የመምራት እድል መነፈጋቸው ነው። ይህ ጉድለት አሁን በእርስዎ አመራር ያለምንም ቅድመ ሁኔታና ግዜ ማባከን መስተካከል ይገባዋል ብየ አምናለሁ። ከአሁን በኃላ እነዚህ ህዝቦች የሌሉበት የኢህአዴግ ፓርቲ መታሰብ የለበትም የሚል እምነት አለኝና ቢያስቡበት። ይህን ደግሞ ስድስት ይበሉልኝ።

ሰባተኛ ብለው እንዲይዙልኝ የምፈልገው ነጥብ ደግሞ በኢትዮ ኤርትራ ጉዳይ ያስመዘገቡት አኩሪ ድልንና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ተግባርን ነው። ለሃያ አመታት አከባቢ በጠላትነት ሲተያዩ  የነበሩ ህዝቦችን አጭር በሚባል ግዜ ተአምር ሰርተው ሰላም አውርደዋል። ኮርቸቦታለሁ። ይህንን የሚያሳልጡ ስምምነቶችዎም አስደስተውኛል። ያ መጥፎ ዝምድና የተፈጠረው በሁለቱ አገሮች መንግስታትና ፓርቲዎች መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ገፈት ቀማሹ በአጠቃላይ የኤርትና የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ በድንበሩ አከባቢ የሚገኝ የኤርትራ፣ የትግራይና የአፋር ህዝብ ነው። መንግስታቱ ሰላሙን ካወረዱ በኋላ እርቁ ማተኮር ያለበት በነዚህ አከባቢዎች ላይ መሆን አለበት። ለእውነተኛ ሰላም መታረቅ የሚገባቸው መንግስታት ብቻ ወይንም ሌሎች ህዝቦች ሳይሆኑ እነዚህ አጎራባች ህዝቦች ሲሆኑ እርቁ እውነተኛና ዘላቂ ይሆናል። የድንበሩ ጉዳይም በሁለቱም መንግስታት እየታገዙ በእነዚህ ህዝቦች ሲከናወን ዘለቄታ ይኖረዋል። ሳይዘገይ ይከናወን። ድንበር የማካለሉ ጉዳይ ተዘሎ ከተሄደ ግን መንግስታቱ ሌላ ግዜ መስማማት ሲያቅታቸው የሚነሳ ሌላ አወዛጋቢ ጉዳይ እንዲሆን እድል መሰጠት የለበትም። የአየር ትራንስፖርት እንደሚጀመር ሰምቼ ፈንድቄአለሁ። ነገር ግን ድሃው የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠቀመው የመኪና ትራንስፖርት ነው። መኪናው ደግሞ እነዚህ ህዝቦች ባሉበት መንገድ ነው የሚያልፈው። ይህ ትራንስፖርት በሰላማዊ መንገድ እንዲከናወን በነዚህ ህዝቦች ሰላም ለማውረድና በተለይ በድንበር አከባቢ ያሉ የሁለቱም አገሮች ህዝቦች ብዙ መስዋእት ስለከፈሉ እነሱን ያካተተ ሰላማዊ ውይይት እንዲቀጥል ማድረጉ ከፍተኛ ግምት እንዲሰጡት እጠይቃለሁ። ሰላሙ በመንግስት ባለስልጣናት መጀመሩ ለዚህ አመቺ ሁናቴን ይፈጥራል ብየ አምናለሁ። ሁለቱ መንግስታት ከተስማሙ ህዝቦቹም ሳይሸማቀቁ ተገናኝተው ችግሮቻቸውን ማስወገድ ይችላሉ። በመንግስታት ብቻ ታጥሮ ከቀረ ግን ባለሃብትና ባለስልጣን ለግዜው ማሳዋና አዲስ አበባ በአየር እየተጓዙ ሊዝናኑ ይችሉ ይሆናል። ግን አያዛልቅም። ስለዚህ ሳይውል ሳያድር ከኤርትራ፣ከትግራይና ከአፋር ህዝቦች የተውጣጡ ተሳታፊዎች  የሚገኙባቸው ከፍተኛ ኮንፈረንሶችን በማካሄድ እርቁን የተሟላ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ የእርቅ ሂደት ከማንኛውም ወገን ለቂም በቀል መወጣጫ ምንም እድል እንዳይሰጥ ከቅርበት መከታተል ይጠበቅቦታል። የኢትዮጵያ ህዝብም ከያለበት ሆኖ ዓይንና ጆሮ በመሆን እንደሚያግዝዎት እርግጠኛ ነኝ። ሁለታችሁም በከፉም በደጉም እየተደጋገፉችሁ እንደምትዘልቁ ስለገለጻችሁልን ልባችን ፍስሃ ተስምቶታል። ይህ አባባል የትላንትናን ቁስል እየነካካ ችግር እንዳይከስት የማድረግ ግዴታዎ ከፍተኛ እንደሆነ ግን በግልጽ አማርኛ መናገር እፈልጋለሁ። ሰላምን እንወዳለን። በጋራ ማደግን እንወዳለን። ነገር ግን ከታሪክ ተውቃሽነት ለመዳን የእርስዎ ዋነኛ ሃላፊነት የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ደህንነትና ጥቅም ማረጋገጥ ነውና ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡት እፈልጋለሁ። በኤርትራ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ እንዲነሳ ትግል መጀመርዎ የሚበረታታ ነው። ይቀጥሉበት። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በኤርትራ በእስር ቤቶችና ኮንቴነሮች እየበሰበሱ ያሉ ኤርትራውያን ወገኖቻችንን ለማስፈታትና በኤርትራ ሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶች እንዲከበሩ፣ ሕገመንግስት እንዲኖርና አስገዳጅ ውትድርናው እንዲያበቃ ያለሰለሰ ጥረት በማድረግ እርቁ የህዝቡን ተጠቃሚነት እንዲያካትት እንዲያደርጉም እማጸንዎታለሁ።

ስምንተኛውና የመጨረሻ አድርገው እንዲይዙልኝ የምፈልገው ወንድማዊ ወቀሳ ነው። የአፋር ህዝብን እንዲያነጋግሩ በሄዱበት ወቅት ከህዝብ ኢህአዴግን አስመልክቶ የቀረበልዎትን ጥያቄ ሲመልሱ የሰጡት መልስ ከእርስዎ የሚጠበቅ አልነበረም። ብእርግጥ በመልሱ ሳይንሳዊ ይዘት እስማማለሁ። አንድ ነገር የሚያድገውና የሚወድቀው በውስጣዊ ይዘቱ ነው። የደርግ ስርዓት ለመውደቅ ዋነኛ ምክንያት የሆነው የደርግ የራሱ ጻረ ዴሞክራስያዊ፣አረመንያዊ፣ ጻረ ህግ ተግባሩ፣ጻረ ህዝብና ፋሽስታዊ ባህርያቱ ወዘተ እንደሆነ አያጠያይቅም። ይህ እንዳለ ሆኖ ደርግ በወደቀበት ወቅት፣ ፍጥነትና አወዳደቅ እንዲወድቅ ያደረገው ግን የኢህአዴግ በጀግንነት የተሞላ የትጥቅ ትግልና የኢትዮጵያ ህዝብ ብርቱ ትግል ነበር። የሰጡት መልስ ይህን ብሽዎች መስዋእት የከፈሉለትን ትግል በቂ ቦታ አልሰጠም። ይህ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀውን ሃቅ በተገቢ ክብደቱ ባለመመለስዎ ደግሞ ብዙዎችን ቅር አሰኝቷል። ቢታረም ጥሩ ነው ባይ ነኝ። የአገር መሪ መሆን ሸክሙ ብዙ ነውና ብዙ ነገር እንዳሸከምክዎት ይገባኛል። የተነሱለት አላማ ቅን ስለሆነ ግን ሁላችንም ሸክምዎን ለማቃለል ዝግጁ ነን። እያንዳንዳችንን ማወቅ ባይችሉም መገናኛ ድልድዮቹ ይዘዋቸው የተነሱ ቅን አላማዎችዎ ናቸውና ካለንበት ቦታ ሆነን እናግዝዎታለን።

ስለዚህ ክቡር ጠቅላይ ሚንስተር ዶክተር አብይ አህመድ የጀመሩትን የሰላም፣ የእርቅ፣ የይቅር እንባባል፣ የዴሞክራሲ፣ የህግ የበላይነት፣ የእድገትና የእንደመር ጉዞ ከሃዲዱ እንዳይወጣ ከዙርያዎ የከበቡትን ያስተውሉ፣ ህግንና ስርአትን እየተከታተለ የሚደግፍዎት ጠንካራ ቡድን ያስቀምጡ። ይዞዋቸው የተነሱ አልማዞች አገር መለወጥ እንዲችሉና እንከን ሳያጋጥማቸው እንዲዘልቁ ሁሌም ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም የሚለውን መፈክር እያስታወሱ ዙርያዎን እንዲያጸዱ በማክበር እጠይቅዎታለሁ። ተስማምተውኛልና ሃሳቤን በእርስዎ ራእዮችና መፈክሮች ላጠቃልል ይፍቀዱልኝ።

ቂም በቀል ይቅር!

ፍቅር ያሸንፋል !

ሰላም ይስፈን !

እድገት እናስመዝግብ !

ዴሞክራሲና ፍትህ ይንገሱ !

ለሕገ መንስታችን ታዛዦች እንሁን !

ሙስና ቀይ መስመራችን ነው !

የቀን ጅቦችን በማንቁርታቸው ይዘን የዘረፉትን እናስመልስ !

ስንኖር ኢትዮጵያውያን ስንሞት ኢትዮጵያ ነን !

አንድ እንሁን እንደመር !

እግዚአብሄር አገራችን ኢትዮጵያንና ህዝቧን ይባርክ !

ተክልየ ከዩ ኤስ አሜሪካ
tekelehaymanottaye@gmail.com